## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም

# ማስተባበያ

# የሱዳን ጦር ከኢትዮጵያ ምድር አልወጣም

የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በሀሰት ዜና በማደናገርና ለጠላቶች በመጥቀም በተካኑ የተወሰኑ ግለሰቦች አማካኝነት የሱዳን ጦር ከያዘው የኢትዮጵያ መሬት በተወሰነ “ ፀረ ወያኔ ጦር ” ጥቃት ለቆ ወጥቷል በሚል የተሰራጨው ዜና መሰረተ ቢስና ሀሰት መሆኑን ኢሕአፓ ለሕዝብ ሁሉ ያስታውቃል፡፡

የወያኔ አገዛዝ ከሱዳን ጋር ተዋውሎ መሬት ሊያስረከብ ገና ሲዳዳው ሁኔታውን አጋልጦ የነበረው ኢሕአፓ በተለይ በቋራ ገፅ በነፍሶ ገበያ አካባቢ ያለውን ሁኔታ በቅርብ እየተከታተለ ያለ ነውና የሱዳን ጦረ ከሰፈረበት የሀገራችን መሬት ለቆ አልወጣም፡፡ ምሽጉን አጠናክሮ ለአሰሳም እየወጣ እየገባ መሆኑም ታይቷል፡፡ ከዚህ ሌላ የሱዳን አራሾች የተያዘውን መሬት ማረስ እስካሁን አልጀመሩም፡፡ በአንፃሩ በዚሁ በቋራ አካባቢ ያርሱ የነበሩ ኢትዮጵያዊ አርሶ አደሮችና የዘመናዊ እርሻዎች ባለቤቶች ወደ ነበሩበት መመለስ በወያኔ ስለተከለከሉ ትራክቶሮችና ሌሎች የእርሻ ቁሳቁሶች ዳዋ ውጧቸው እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተወሰነ ደረጃ ሲደረግ የነበረው የሕዝብ ተቃውሞም አሁንም መደራጀትና መደገፍ እንዳለበት ሁኔታው ያሳያል፡፡

ከሀዲው የወያኔ አገዛዝ መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን ካደ፤ ኢትዮጵያዊ አራሾቸ በሱዳን መያዛቸውንና መታሰራቸውን ካደ ፤ ሀቁንም ለመሸፈን ብዙ ሀሰቶች አዥጎደጎደ ፡፡ ዛሬ ሀቁ ታውቆ ሲወገዝ ደግሞ በፀረ ወያኔነት ሽፋን ያሰለፋቸው ቅጥረኞቹ በግለሰብና በኮሚቴ ወይም ቡድን ስም የሱዳን ጦር በኢትዮጵያ መሬት የለም ብለው ትጥቅ አስፈቺና አደናጋሪ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ/ዜና እያሰራጩ ናቸው፡፡ ይህ መጋለጥና ሀቁ መታወቅ አለበት፡፡ የሱዳን ጦር አሁንም በኢትዮጵያ መሬት ሰፍሯል--ያባረረውና አጥቅቶ ያስወጣው ኃይል የለም፡፡ በዚህ ላይ ጦር አለን፤ በዚህ በቋራ ምድር እየተንቀሳቀስን ነው ወዘተ ስለሚሉት ሆነ ስለሚያስወሩት መተቸት ባንፈልግም በመሰረቱ በሀገራችን መሬት የሰፈረውን የሱዳን ጦር ያባረረው ኃይል ግን የለም፡፡ ማባረሩ ገና ትግልን የሚጠብቅ ግዳጅ ነውና ለወያኔና ለሱዳን የሚጠቅም የሀሰት መረጃን የሚያቀርቡትን ሁሉ ሕዝብ ሊነቃባቸውና ሊያወግዛቸው ይገባል፡፡

**የውጭ ወራሪን ለመቋቋም አብረን እንነሳ!!**
**የወያኔ ቅጥረኞች ይጋለጣሉ!!**

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217; Fax : (202) 291-7645

**E-mail** ESPIC@aol.com

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France
**Website:** http://www.EPRP.com